በየካ ክ/ከ/ለ ከተማ ወረዳ **08** ብሩህ ተስፋ ጉድኝት ማዕከል የወጣቶች ገነት ቅ/አ/አ/ደ/ት/ቤት አማርኛ ቋንቋ ት/ት የ **6** ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና

2016 ዓ.ም

ስም ---------- ክፍል ------ ቁጥር ---

ታህሳስ 11/04/2016

የተፈቀደው ጊዜ ፡- 1፡00 ሰዓት

ንባብ

ክረምት የልቡን ሰርቶ «እንዲህ ነኝ እኔ ወንዱ! ; እያለ እየተጎማለለና እየፎከረ «ቆይ ደግሞ እንገናኛለን; እያለ እየዛተ እያስፈራራ ስፍራውን ለጠቢ ፀሐይ እየለቀቀ ጓዙን ጠቅልሎ መሄድ ጀምሯል። ተነፋፍቀው የሰነበቱ መሬት እና ፀሐይ ቶሎ የሚጣጋቡ አይመስሉም። ጨረሯን ሙሉ በመሉ መሬት እንዳትደርስ ከልክሏት ከመሬት ጋር አኮራርፏት የከረመው ደመና ሲገፋ ፀሐይ በብቸኝነት የምትኩራራ ትመስላለች። አዲስ አበባን የኩበቡት ተራሮች በአደይ አበባ አሸብርቀው ጀንበሯ እስክታዘቀዝቅ በሚሸኟት ደማቅ ቀለማት ተውበው ከተማቸውን ዙሪያውን ከበው የሚደበቁ ይመስላሉ። መስከረም ስያልቅ «መስከረም ጠባዬ » እያሉ ይዘፍናሉ። ወፎች እልልታውን ያስነኩታል።

ከድሮ አውሮፕላን ማረፊያ ባሻገር በጀርባው የረጲንና የመናፈሻን ተራራ ተገን አድርጎ ችምችም ብሎ የበቀለውን ደን እሱም የአደይ አበባውን የከበሮ ድልቂያና ጭብጨባ የሚከተል የራሱን እስክስታ ጀምሯል። ወደ አንድ ወገን ጋደል ይልና ቀና እንደገና ወደሌላ ወገን ጋደል -------- አንድ ላይ። በተለይ አንጋጠው ሲመለከቱት በተለይ ብሶት ያለበትን ሰው ያባብላል። «ã ረ ጥራኝ ዱሩ » በሚል አይነት።

የአዲስ አበባ ግርግር መሸትም ሲል አያባራም ፣ እንዲያውም ይብስበታል። እግረኛው መኪናው ይርመሰመሳል። የመንገድ ዳር መብራቶች አዲስ አበባን ማድመቅ ጀምረዋል። ልጆች «የሰማይ አንፖል» እያሉ የሚጠሯት ጨረቃ ግዙፍ ሎል ይመስል ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ አድማሱ ጥግ ልጥፍ ብላ ትታያለች። ሚኪያስ ፍኖት የሳሎኑን ስስመጋረጃ ገለጠና ወደውጪ ተመለከተ። ከግንቡ አጥር ውጭ ሊታየው አልቻለም። አረንጓዴ ቀለም የተቀባው የአጥሩ ብረትበር እንደተዘጋ ነው። የግቢው ልዩ ልዩ አበቦች የጀንበሯን ማሽቆልቆል የሚቃወም ሰልፈኛ መስለው ተርታውን ተሰልፈው ግራቀኝ ይወዛወዛሉ።

የሚልኪያስ አይኑ ሊደፈርስበት የቻለውን ሁሉ እስኪበቃው ቃኘ እና ሰዓቱን ተመለከተ። አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ምንጭ፡- ሰለሞን ለማ 1982። አዲስ አበባ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ፣ከገፅ 169-170 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ።

I. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከላይ በተሰጠው ምንባብ መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ

--1. «ለጠቢ» ለሚለው ቃል የሚስማማው ፍቺ የትኛው ነው?

ሀ. ከበጋ ውጭ ግንቦት ለ. ከበልግ ውጭ ሰኔ

ሐ. ከክረምት ውጭ መስከረም መ. ከፀደይ ውጭ ህዳር

--2. የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀፅ ስለምን ይናገራል?

ሀ. ስለ ክረምቱ ማለፍ ሐ. ስለ ክረምቱ መግባቱ

ለ. ስለ ክረምቱ አስቸጋሪ መሆን መ. ስለ ክረምቱ እየከበደ መምጣት

--3. በምንባቡ ውስጥ በትልቁስል የተመስለው ምንድ ነው?

ሀ. ጨረቃ ለ. ፀሐይ ሐ. አዲስ አበባ መ. መሬት

--4. ምንባቡ

ሀ. ተረኪ ለ. አመዛዛኝ ሐ. ገላጭ መ. አስረጂ

--5. በመጀመሪያው አንቀፅ «ቆይ ደግሞ እንገናኛለን» የሚለው ሀሳብ የቀረበው በምን ዐይት ነው?

ሀ. በመተሳሰብ ለ. በዛቻ

ሐ. በሰላምታ መ. በመሰናበት

--6. እንደ ምንባቡ ሃሳብ የጀንበር ማሽቆልቆል ምንን ያመለክታል

ሀ. ቀኑ መደመኑን ለ. ቀኑ መጨለሙን

ሐ. ቀኑ ተስያት መሆኑን መ. መምሸቱን

--7. ቃኘ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺው ---------- ነው?

ሀ. ተመለከተ ለ. ዞረ ሐ. ቀና መ. ገለጠ

<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደየ አጠያየቃቸው ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ</u>

--8 ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የወል ስም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሰለሞን ለ. ወንበር ሐ. ተራራ መ. ጠረጴዛ

-------9. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ውስጠ ግንድ ቅጥያ ያለው ቃል የትኛው ነው?

ሀ. ሰዎች ለ. ቀያይ ሐ. ሰማይ መ. የኢትዮጵያ

--10. ከሚከተሉት መካከል ከጊዜ ተውሳከ ግስ የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. ዛሬ ለ. ቅድም ሐ. ነገ መ. ክፋኛ

--11. ልጁ እያጠና ነው። የሚለው ዓ.ነገር የ -------- ጊዜን ያመለክታል

ሀ. የትንቢት ለ. የታላፊ ሐ. የአሁን መ. የነገ

--12. በመጥበቅና በመላላት ሲነገር ሁለት የተለያየ ትርጉም የሚሰጠው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ስም ለ. ስንዴ ሐ. ጥፍር መ. ጨረቃ

--13. ---------- ጎበዝ ተማሪ ነው። በባዶ ቦታው ተስማሚው ተውላጠ ስም የቱ ነው?

ሀ. እሷ ለ. እሱ ሐ. እኔ መ. እነርሱ

--14. ሊዲያ ቢጫ «<u>ቀሚስ</u>» አላት። በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ ቅፅል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሊዲያ ለ. ቀሚስ ሐ. ቢጫ መ. አላት

--15. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የክርክር ዝግጅት መመሪያ ያልሆነው የቱ ነው

ሀ. ርዕሰ መምረጥ ለ. መረጃ ማሰባሰብ

ሐ. የአድማጭን ማንነት መለየት መ. ራስን ማስተዋወቅ

--16. ቃላት ከገቡበት ዓ.ነገር አንፃር የምንሰጠው ፍቺ ---------- ይባላል።

ሀ. ተቃራኒ ፍቺ ለ. ተመሳሳይ ፍቺ

ሐ. ዐውዳዊ ፍቺ መ. እማሬያዊ ፍቺ

--17. የአንቀፅ መሰረታዊ አካላት የምንላቸው የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ባለቤትና ተሳቢ ለ. ታይለ ቃልና መዘርዘር

ሐ. ነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ መ. አ.ነገር እና ሀረግ

--18. «አንተ፣ አንቺ፣እናንተ» የሚሉት ተውላጠ ስሞች ስንተኛ መደብ ናቸው?

ሀ. ሶስተኛ መደብ ለ. ሁለተኛ መደብ

ሐ. አንደኛ መደብ መ. መደብን አይገልፅም

--19. ተማሩ የሚለው ቃል በምን ዖታ ተገልፃል?

ሀ. በአነስታይ ለ. በተባሳታይ

ሐ. ዖታ አልገልፅም መ. ሁሉም መልስ ነው

--20. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በነጠላ ቁጥር የተገለፀው የቱ ነው?

ሀ. ልብሶች ለ. ወንበሮች ሐ. መኪና መ. ተማሪዎች

--21. አቤል ኳስ እየተጫወተ ነው። በሚለው ዓ.ነገር የተሰመረበት ቃል ------- ነው።

ሀ. ግስ ለ. ቅፅል ሐ. ስም መ. ተውላጠ ስም

--22. ምዕላድ በስንት ይከፈላል?

ሀ. በሁለት ለ. በአራት ሐ. በአምስት መ. በሶስት

--23. የቃላዊ ግጥም ደራሲ ማን ነው?

ሀ. ጥላሁን ገሰሰ ለ. ማህበረሰቡ ሐ. ሀዲስ አለማየሁ መ. አይታወቅም

--24. ያችን ማጭዴን ሆዷን አሚታል

እየቆረጠ ያጋድማታል

ይህ ቃላዊ ግጥም በ ---------- ጊዜ የሚቀርብ ነው

ሀ. በአጨዳ ለ. በውቂያ ሐ. በቀረርቶ መ. በሀዘን

--25.የግጥም አንድ መስመር ምን ይባላል?

ሀ. ሐረግ ለ. ስንኝ ሐ. ቤት መ. አንጓ

--26.ስንኝ ውስጥ የመጨረሻ ቃል የመጨረሻ ፊደል ---------- ይባላል።

ሀ. ቤት መድፊያ ለ. አንጓ ሐ. ቀለም መ. ስንኝ

--27. የስንኝ እኩሌታ ምን ይባላል?

ሀ. ሀረግ ለ. ቤት ሐ. ቀለም መ. ስንኝ

--28.ከአለባበስ ይቀደዳል ከአነጋገር ----------። በሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ ባዶ ቦታውን የሚያሟላው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ያስታውቃል ለ. ይፈረዳል ሐ.ይሳሳታል መ. ይዋሻል

--29. በውስጡ ሁለት እና ከሁለት በላይ ግሶችን የሚይዝ ዓ.ነገር ምን ይባላል?

ሀ. ተራ ዓ.ነገር ለ. ድርብ ዓ.ነገር ሐ. ድብልቅ ዓ.ነገር መ. ደርብ ድርብርብ

--30. ሰማዩ በጣም ጠቁሯል ---------- ምናልባት ከሰአት በኋላ ሊዘንብ ይችላል።

በባዶ ቦታ ላይ የሚገባው ትክክለኛ ስርአተ ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ. አራት ነጥብ ለ. ድርብ ሰረዝ ሐ. ነጠላ ሰረዝ መ. ትምህርተ አንክሮ

--31. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ባለንብረትን የሚልፀው ቃል የቱ ነው?

ሀ. መፅሐፋችን ለ. መፅሐፎች ሐ. እነመፅሐፍ መ. መፅሀፍት

--32.የአንቀፅን ቅርፅ የሚወስንልን ምድነው?

ሀ. ግጥም ለ. ኃይለቃል ሀ. መዘርዝር መ. ቢጋር

<u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የሆነውን ምረጡ</u>

--33. ማጠራቀም

ሀ. መበተን ለ. ማከማቸት ሐ. ማስፋፋት መ. መቅረፅ

--34. ሀሴት

ሀ. ሀዘን ለ. ደስታ ሐ. ለቅሶ መ. ንዴት

--35. መቅሰም

ሀ. መውጣት ለ. መደሰት ሐ. መማር መ. ማየት

--36.አመል

ሀ. ጥሩ ለ. ክፉ ሐ. ባህሪ መ. ምላሽ

<u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ የሆነውን ምረጡ</u>

--37. መብዛት

ሀ. መበርከት ለ. መውጣት ሐ. ማነስ መ. ግዙፍ

--38.ዘመናዊ

ሀ. ባህላዊ ለ. ቆንጆ ሐ. እውነት መ. አሁን

--39. በአንድነት

ሀ. በግል ለ.በጋራ ሐ. በነቂስ መ. በህብረት

--40. ማበረታታት

ሀ. ማጎልበት ለ. ማፍራት ሐ. ማናናቅ መ. ማጣት

አዘጋጅ ፦ ወጣቶች ገነት ት/ቤት